የሰ/መ/ቁ. 43005

ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ አውግቸው እርገጤ
2. ወ/ሮ ማህደር ቢተው
3. አቶ አደራጀው ዘውአለ
ሁሉም ከጠበቃ ሳሕሉ ሀብቴ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 ስር የተመለከተውን መሰረት በማድረግ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካቾች ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ስላመለከቱ የቀረበ ነው፡፡

የአመልካቾች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ዘርዝረዋል፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካቾችን አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተያዘው የጉዲፈቻ ውል ይፅደቅልኝ ጥያቄ ሂደት ውስጥ ሐሰተኛ አቤቱታና አስተያየት በማቅረብና ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት ሞክረዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሕጻን ሂክማን ኢብራሂምን ተቀብሎ የሚያሳድጋት ብርሃን ሕይወት የሕጻናትና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት አቶ አውግቸው እርገጤ ወኪል ለሆኑላቸው ጀርመናዊያን ባልና ሚስት በጉዲፈቻ ለመስጠት ያደረገውን ውል ፍርድ ቤት ለማስፀደቅ ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦለት የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጥበት ችሎቱ ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ ለሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ቡድን መሪ ለሆኑት ላሁኑ ሁለተኛ አመልካች ቀርቦላቸው የጉዲፈቻ ማንነት ሲመረመር ሕጻናት ማሳደጊያው ተግባሩን እንዳይቀጥል በፍትሕ ሚኒስቴር እንደታገደ በመታወቁ ሕፃኗ በቅድሚያ ሕጋዊ ለሆነው የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ባሁኑ ሦስተኛ አመልካች በሚተዳደረው የእናት ዓለም ሕፃናት ማሳደጊያ እንደተላለፈች፣ ከዚህም በኂላ ያሁኑ አንደኛ አመልካች ከአዲሱ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ጋር የጉዲፈቻ ውል ፈፅመው ሁለተኛ አመልካች አንደኛ አመልካች ሕፃኗን አዲስ ከተረከበው ድርጅት ጋር ያደረጉት የጉዲፈቻ ውል እንዲፀድቅ ታህሳስ 07 ቀን 2001 ዓ/ም አስተያየት መስጠታቸውን ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካቾችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት ሊያስተላልፍ የቻለው በተዘጋና እንደገና አስተያየት እንዲሰጥ ባልተጠየቀበት መዝገብ አስተያየት የተሰጠው ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ መሆኑን፣ አንደኛ አመልካች ብርሃን

ሕይወት የሕጻናት እና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት መፍረሱን አያውቁም ነበር ተብሎ ታህሳስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በኋላ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት መዝገብ ውሳኔ የተሠጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 ይዘት ሲታይ በዳኝነት ስራ ላይ ወንጀል ሲፈፀም ፍርድ ቤቱ ጥፋቱ በተደረገበት ጊዜ በያዘው የፍትሐብሔር መዝገብ ወዲያውኑ ቀጥታ ቅጣት ሊያስተላልፍ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መንገድ ቅጣት ሊያስከትል የሚችለው ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 452(1) ስር የተመለከተው በተከራካሪ ወገን የሚሰጠው ሐሰተኛ ቃል ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠያቂነት የሚመጣው ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ቀርቦ እውነት እናዲናገር ታዞ በፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል በሚወሰን ጭብጥ ላይ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮችን በሚመለከት እያወቀ ሐሰተኛ ቃል የሠጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

የድንጋጌው አይነተኛ ዓላማ የዳኝነትን ክብርን፣ የዳኝነት አስተዳደርን የሚነካ፣ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ ድርጊት መከላከልና እውነትን መሰረት ያደረገ ፍርድ እንዲሰጥ ማስቻል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህንን ለማሳካት ደግሞ ፍርድ ቤት ድንጋጌውን ሲያስፈጽም በድንጋጌው ስር የተመለከቱ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች መሟላታቸውንና በተገቢው ማስረጃ መደገፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ የወንጀል ባሕርይ ያለው እንደመሆኑ መጠን በወንጀል ስነ-ሕግ ተቀባይነት ያላቸው መርሆዎችንና በሕገ መንግስቱ ውስጥ የተካተቱትን መሰረታዊ መብቶችን ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ ባንድ መዝገብ ሁለት ጊዜ ውሳኔ የተሠጠባቸው ሲሆን በመጀመሪያው ብይን ይኸው አመልካች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት ድርጊት እንደሌለ ተገልፆ በነጻ ከተሰናበቱ በኋላ እንደገና እንዲቀጡ መደረጉ ተገቢውን ስርዓት በተከተለ ሁኔታ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ባንድ የወንጀል ድርጊት ነጻ ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በዚያው ጉዳይ እንደገና ሌላ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጎ የሚቀጣበት አግባብ የለምና፡፡ ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተም አመልካች ሰጡ የተባሉት አስተያየት በሕጉ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ለሕፃን ጥቅም ማስጠበቅ መሆኑ የሚገለፅ እስከ ሆነ እና ፍርድ ቤቱ አስተያየቱ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ያለመሆኑን በመመርመር በጉዲፈቻ ውል መፅደቅ አለመጽደቅ ላይ ተገቢውን ውሳኔ የሚሠጥበት ከሚሆን በስተቀር ሐሰተኛ ነው ተብሎ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል አይሆንም፡፡ ከሁሉም በላይ ሁለተኛ ተጠሪ አስተያየት ሰጡ የተባሉበት ድርጅት የፈረሰ መሆኑን እያወቁ አስተያየት መስጠታቸው በእርግጠኝነት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ አመልካች ሐሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ሊባሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ሦስተኛ አመልካችን በተመለከተም የተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ስንመለከተው ይኸው አመልካች ተፈፀመ ለተባለው ድርጊት የነበራቸው የድርጊት ተሳትፎ ምን እንደሆነና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል የሚያሳይ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ የገለፀው ነገር የለም፡፡ አንድ ሰው ደግሞ በወንጀሉ ድርጊት የነበረው ተሳትፎ ባግባቡ ሳይረጋገጥ የሚቀጣበት ሕግ የለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊ ስርዓቱን መሰረት ያላደረገ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 እና በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 452(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የማያሟላ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128857 ታህሳስ 20 እና 22 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75302 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናውን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካቾችን በነፃ አሰናብተናል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ